# መጽሐፈ ነህምያና መሪነተ - ክፍል ፪

1. <u>መሪ ከሁሉ በፊት አስፈላጊ ለሆኑ ነገሮች ቅድሚያ ይሰጣል...</u>

- አገልጋይ መጻሕፍትን ማጥናት፣ መስበክና ሕዝቡ ምን ማድረግ እንዳለበት መናገር ብቻ ሳይሆን ሕዝቡ/ምዕመናኑ ለሚጋፈጧቸው ችግሮችና ለሚፈልጉት ወይም ለሚያስፈልጓቸው ነገሮች እውቅና ከመስጠት ጋር መፍትሔ ማበጀት ይጠበቅበታል፡፡
- ለዚህም ለቤተ ክርስቲያናችን አስፈላጊው ነገር ምንድን ነው? መንፈሳዊ ነገር ነው? ገንዘብ ነው? የገንዘብ አያያዝ ችግር ነው? የኢትዮጵያስ ችግር ምንድን ነው? በዙሪያችንስ ላሉ ነገሮች ሁሉ ትኩረት እየሰጠን ነው? በማኅበረሰባችንም ሆነ በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለው ችግር ምንድነው? ቢያንስ ስለነዚህ ጉዳዮች በቂ ግንዛቤ አለኝ? ብሎ ራሱን መጠየቅ ይገባዋል፡፡
- መሪ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን አምኖ በግልጽ የተቀበለ፤ ላየው ነገር ሁሉ ትኩረት የሚሰጥ ማለት ነው፡፡

2. <u>መሪ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ሁሉ በግሉ የሚያሳስቡት ሰው ነው፡፡</u>

- ነህምያ የተጠራው ቅጥሮቹን እንዲሠራ ቢሆንም ከሁሉ አስቀድሞ ግን ስለፈራረሱት የቀደሙት ቅጥሮች አለቀሰ፡፡ እኛም እንዲሁ አንድ ነገር ከማድረጋችን በፊት ሊያሳስበን ይገባል፡፡
- ነህምያ አለቀሰ፣ አዘነና ጾመ፡፡ እኛ የግል ችግር ሲገጥመን ስንት ቀን እንጾማለን? ምናልባት ሦስት ወይም ሰባት ቀናት? ነህምያ ግን አራት ወር ጾመ፡፡ ለዚያው የጾመው ከአገር ውጪ በቤተ መንግሥት እየኖረ ነው፡፡
- ስለ ኢየሩሳሌም ቅጥሮች መፍረስና ስለ ወገኖቹም ሲሰማ ስለችግራቸው ትኩረት ሰጠ ይመለከተኛልም አለ እንጂ ሰነፎች ናቸው፣ ለምን መልሰው አልሠሩትም... በማለት አልፈረደባቸውም፡፡

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፪

2. <u>መሪ አስፈላጊ የሆኑ ነገሮች ሁሉ በግሉ የሚያሳስቡት ሰው ነው…</u>

- ዛሬ እንደሚታየው በቤታችንም ሆነ በቅርባችን ባለ ጉዳይ ሳይቀር ግዴለሽ ሆነን የምንገኝበት ደረጃና ሁኔታ አለ፡፡
- ይህ ዓይነት ማንነት የሚመነጨውም ምንም ነገር አትንገሩኝ፣ ምንም ጭቅጭቅም ሆነ ንትርክ አልፈልግም ከሚል ደንታ ቢስነት ነው፡፡
- ወላጆች ስለቤተሰባዊ ሕይወታቸው ያለባቸውን ኃላፊነት ዘንግተው ጉዳዩን የቤተ ክርስቲያን አባቶች ጉዳይ ነው ማለት ከጀመሩ አደገኛ የነገር ፍጻሜ ነው፤ በዚህም አካሄድ የተነሳ እጅግ የተበላሹ ልጆችን በቤተ ክርስቲያን ብናይ እንኳን መደነቅ የለብንም፡፡ ቤተ ክርስቲያን የሚጠበቅባት በአጠቃላይ አቅጣጫ ማሳየት ነው፡፡ ወላጆች ስለ ልጆቻችን የማንጸልይ፣ የማንጾም ከሆን ማንም ጤናማ ሊሆን እንደማይችል ስለ ልጆቻችንም ከኛ በላይ ማንም ሊጸልይላቸውና ሊጾምላቸው እንደማይችል ማስተዋል አለብን፡፡

3. <u>ከልቡ የሆነ መሪ ችግሮቹን ሁሉ ወደ እግዚአብሔር ያቀርባቸዋል፡፡</u>

- የርስ በርስ ተግባቦች ችግሮቻችንን እንዴት እንፈታለን?
- ከልጆቻችን፣ ወላጆቻችን፣ የትዳር ጓደኞችን፣ የሥራ አለቆቻችን… ወዘተ ጋር ያሉ ችግሮችን እንዴት እንፈታቸዋለን? እንዴትስ እናስተናግዳቸዋለን? ከእግዚአብሔር ጋር ስለ ችግ(ሩ)ሮቹ ከመነጋገራችን በፊት ካገኘነው ሰው ጋር እናወራለን፣ እንፈርዳለን፣ እናማለን? ወይስ…?

# መጽሐፈ ነህምያና መሪነት - ክፍል ፪

4. <u>ከልቡ የሆነ መሪ አስፈላጊውን ነገር በራሱ ለማሟላት ይነሳሳል ራሱን የመፍትሔ አካል ያደርጋል፡፡</u>

- ለምን ይህን አለ? ይህ ንጉሥ ኢየሩሳሌምን ባቃጠላት ንጉሥ እግር የተተካ አይደለም? ነህምያ ያለውን ሥልጣን ሁሉ የሚጠቀምበት ብቸኛ ሰዓት ሲገጥመው እግዚአብሔር ለዚህ ጉዳይ በዚህ ሰዓት ወደዚህ ቦታና ሥልጣን አጥቶኛል ብሎ እግዚአብሔር ሆይ! እንደ አስቴር ለእኔ ለባሪያህ በንጉሡ ፊት ምሕረትን ስጠኝ አለ፡፡

**ማጠቃለያ**

- መሪ እግዚአብሔር በተወሰነ ጊዜ፣ ሁኔታ የርሱን ራእይ እንድናውቅ፣ ምልክቱን እንድንረዳ፣ ስለ ሌሎች ጥልቅ የአሳቢነት ልቦና የሰጠው፣ ስለሌሎች የሚጠነቀቅ በጊዜው የምንደገፍበት ሰው ማለት ነው፡፡ ይህም ሁላችንን እንጂ በሥልጣን ወንበር ላይ የተቀመጡትን ብቻ የሚመለከት አይደለም፡፡
- ነህምያ ንጉሥ፣ ነቢይ፣ ካህን /ቄስ አልነበረም፡፡ ባለው ሁሉ ግን ተጠቅሞ ሌሎችን የሚንከባከብና ስለሌሎች የሚጠነቀቅ ነበር፡፡
- ነህምያ ለወገኖቹ ብቻ ሳይሆን ለእግዚአብሔር ነገርም የሚጠነቀቅና የሚያስብ ሰው ነበር፡፡ እግዚአብሔርም በሚያስደንቅ ሁኔታ ተጠቀመበት፡፡

# <u>መጽሐፈ ነህምያና መሪነተ - ክፍል ፬</u>

<u>ማስታወሻ - የቤት ሥራ</u>

- በሳምንት ከአንድ ጊዜ በላይ የምታገኙአቸውን አምስት ሰዎች ስም ጻፉ፡፡ ጤና፣ ገንዘብን፣… በተመለከተ ምን ይገጥማቸዋል?... ነግረሽኝ ነበር እንዴት ሆንክ … እንበላቸው? መድኃኒት ወስጃለሁ …. ግን ጨጓራዬን ነካኝ …. እያሉ እንዲያቃስቱ… በመፍቀድ ከልብ ተነጋገሩ፡፡
- ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጋት ምንድን ነው? ለአካባቢዬ ማኅበረሰብስ? ለቤተሰቤ…? ለአገሬስ? እንበል፡፡ እግዚአብሔር የሚጠቀምብን በዚህ መንገድ ነውና፡፡
- አስቀድመን የሚያስፈልገንን በማወቅ፣ በግል ስለ ጉዳዩ ትኩረት በመስጠት፣ ጉዳዩን ወደ እግዚአብሔር በማቅረብ፣ መፍትሔና ለውጥ ለማምጣት ፈቃደኛ ወይም ዝግጁ ሆነን እንገኝ፡፡

